# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበ የ2016 በጀት ዓመት የበጀት መግለጫ

አህመድ ሺዴ

የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር

ሰኔ 1/2015 ዓ.ም.

# Budget Speech

**የተከበሩ አፈ ጉባኤ**
**የተከበራችሁ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባላት**

የሚኒስትሮች ም/ቤት ግንቦት 29 ቀን 2015 ዓ.ም. ባካሄደው መደበኛ ስብሰባው የ2016 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት አጠቃላይ በጀት 801.65 ቢሊዮን ብር እንዲሆን በመደገፍ በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲጸድቅ መቅረቡ ይታወሳል፡፡ ዛሬ በዚህ ም/ቤት የተገኘሁትም በየዓመቱ እንደሚደረገው ይህ የቀረበው የ2016 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት ረቂቅ በጀት የተመሠረተበትን ኢኮኖሚያዊ ታሳቢዎችና በጀቱ ትኩረት ያደረገባቸውን ፕሮግራሞች በሚመለከት ለተከበረው ም/ቤት ዝርዝር መግለጫ ለማቅረብ ነው፡፡ ይህ የማቀርበው መግለጫም ተደግፎ ስለቀረበው በጀት በፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) መሠረት የተዘጋጀ ማብራሪያ ነው፡፡

**የተከበሩ አፈ ጉባኤ**
**የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት**

መንግስት ባለፉት ዓመታት በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም በዋና ዋና አጠቃላይ ኢኮኖሚ (የማክሮ ኢኮኖሚ)፣ መዋቅራዊና እና በዘርፍ የታቀዱ ማሻሻያዎችን በትጋት ተግባራዊ በማድረግ ትልልቅ ለውጦች እንዲመዘገቡ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ መቆየቱ የሚታወቅ ነው፡፡ እንደ ሀገር የገጠሙንን መጠነ ሰፊ ችግሮች በጽናት እና በስልት በመቋቋም እነዚህን የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች (ሪፎርሞች) ተግባራዊ በማድረግ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገቱን ቀጣይነት ማረጋገጥ ከመቻሉም በላይ ኢኮኖሚው ተጽእኖዎችን የመቋቋም አቅም (resilience) እንዲገነባ አስችሏል፡፡ በዚህም መሠረት ባለፉት ዓመታት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የ6.1 በመቶ አማካይ ዕድገት አስመዝግቧል፡፡ ይህም ዕድገት የመነጨው በግብርና፣ በኢንዱስትሪና በአገልግሎት ዘርፎች በተመዘገበው መጠነ ሰፊ ዕድገት ነው፡፡ ይህ የተመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገትም የዜጎች የነፍስ ወከፍ ገቢ በ2011 በጀት ዓመት ከነበረበት 983 የአሜሪካን ዶላር በ2014 ወደ 1218 የአሜሪካን ዶላር ከፍ እንዲል አድርጓል፡፡ ሆኖም የኢኮኖሚ ዕድገቱን በ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ በተቀመጠው የ10 መቶ ዕድገት ግብ መጠን ማሳደግ አሁንም ከፍተኛ ጥረትን

የሚጠይቅ ሲሆን፣ ባለፉት ዓመታት የተከሰቱት ተደራራቢ ቀውሶች (shocks) ይህ ግብ እንዳይሳካ ዋና ምክንያት ሆነዋል።

የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ትግበራው እንዲሁም የኤክስፖርት አፈጻጸማችን ከዓመታት ማሽቆልቆል በኋላ ዕድገት እንዲያሳይ ማድረጉ ሌላው ስኬት ነው። የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትና በውጭ ሀገር የሚኖሩ ዜጎች ወደ ሀገር የሚልኩት ገንዘብ (remittance) ገቢም እንዲሁ በኮቪድ ወረርሽኝ ተጽእኖ ከነበረበት ዝቅተኛ አፈጻጸም በማንሰራራት ዕድገት አሳይቷል። በመሆኑም የመርቻንዳይዝ (የሸቀጦች) ኤክስፖርት ገቢ የ15 በመቶ አማካይ ዕድገት በማስመዝገብ ለመጀመሪያ ጊዜ በ2014 በጀት ዓመት 4.1 ቢሊዮን ዶላር ገቢ ለመሰብሰብ ተችሏል። እንዲሁም በ2014 በጀት ዓመት 7.5 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገር የላኩ ሲሆን፣ የውጭ ሀገር ቀጥታ ኢንቨስትመንት ደግሞ በሶስቱ የሪፎርም ዓመታት የ3.1 በመቶ አማካይ ዕድገት አስመዝግቧል። ይህ አፈጻጸም መልካም የሚባልና በአስቸጋሪ ወቅት የተመዘገበ ቢሆንም፣ የንግድ ሚዛን ጉድለታችንን በራሳችን አቅም ለመሸፈን አሁንም የኤክስፖርትን አፈጻጸም ከዚህ በላቀ ደረጃ ላይ ማድረስ የግድ አስፈላጊ ነው።

የመንግስት ልማት ድርጅቶችን ለማሻሻል ተግባራዊ የተደረጉ የሪፎርም ሥራዎች የድርጅቶቹ የሥራ አፈጻጸም እንዲሻሻል ከመርዳቱም በላይ ተወዳዳሪ እንዲሆኑና ተጨማሪ ሀብት እንዲፈጥሩ የሚያስችል መሠረት ተጥሏል። በተደረጉት ሪፎርሞች የአብዛኛው የመንግስት ልማት ድርጅቶች ገቢና ትርፍ መጠን ያደገ ሲሆን የኮርፖሬት አመራራቸውም እየተሻሻለ ይገኛል። ከዚህ በተጨማሪ ተግባራዊ የተደረጉ የማሻሻያ ሥራዎችን ለመግለጽ ያህል፣ በቴሌኮም ዘርፍ የነበረውን የመንግስት ሞኖፖሊ በማንሳት ለግል ዘርፍ ተሳትፎ ክፍት በማድረግ (telecom sector liberalization) በዘርፉ ተወዳዳሪነት እንዲኖር ማድረግ ተችሏል። በዚህም መሠረት ከኢትዮ ቴሌኮም በተጨማሪ ለአንድ ዓለም ዓቀፍ የቴሌኮም ካምፓኒ ፈቃድ በመስጠት ሥራ እንዲጀምር የተደረገ ሲሆን፣ ሀገሪቱም ከዚህ ፈቃድ ክፍያ በውጭ ምንዛሬ 1 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ እንድታገኝ ማድረግ ተችሏል። እንዲሁም፣ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት

ሆልዲንግ ተቋቁሞ ሥራ የጀመረ ሲሆን፣ ይህም የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተጨማሪ ሀብት እንዲፈጥሩ እና የጋራ ኢንስትመንት ለማስፋፋት የሚያስችል ይሆናል፡፡ በተጨማሪም፣ ከፍተኛ የዕዳ ጫና ያለባቸውን የመንግስት የልማት ድርጅቶች ዕዳ የሚረከብና የሚያስተዳድር የዕዳና ሀብት አስተዳደር ኮርፖሬሽን የተቋቋመ ሲሆን፣ ይህም የመንግስት የልማት ድርጅቶቹ የፋይናንስ ጤንነትን በማሻሻል ወደ ትርፋማነት እንዲሸጋገሩ የሚረዳ ከፍተኛ እርምጃ ነው፡፡ እንዲሁም የመንግስት ልማት ድርጅቶችን ተወዳዳሪነት እና ውጤታማነት ለማረጋገጥ ድርጅቶቹ የሚመሩበት ህግ በጥናት ላይ በመመሥረት በርካታ ማሻሻያዎች ተደርገውበት ረቂቅ ህጉ በም/ቤቱ እንዲጸድቅ ቀርቧል፡፡ በአጠቃላይ የመንግስት ልማት ድርጅቶችን የኦፐሬሽንና የአመራር (governance) አቅምን የሚያሻሽሉ በርካታ የሪፎርም እርምጃዎች ተግባራዊ በመደረጋቸው የድርጅቶቹ አፈጻጸምና ተወዳዳሪነትን ማሻሻል ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል ቀልጣፋና ውጤታማ የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓትን በመቅረጽ ተግባራዊ ማድረግ የተቻለ ሲሆን፣ የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥርዓቱን ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችሉ በርካታ ተግባራት በመከናወን ላይ ናቸው፡፡ ከነዚህም መካካል የመንግሥት ግዢና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ማሻሻያ ተዘጋጅቶ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲጸድቅ ቀርቧል፡፡ እንዲሁም የአዋጁ ማስፈፀሚያ ረቂቅ መመሪያዎች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ ለማዋል ቅድመ ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል፡፡ የመንግስት ግዥ ስርዓትን በማዘመን ቀልጣፋ፣ ግልፅና ውጤታማ ግዥዎችን ለማከናወን የሚያስችል በቴክኖሎጂ የተደገፈ ስርዓት ለምቶ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ በዚህም መሰረት የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት ግዢ ሥርዓት (Electronic Government Procurement) በ73 የፌደራል መ/ቤቶች ላይ ተግበራዊ ተደርጓል፡፡ በቀሩት መ/ቤቶችም ትግበራው በቀጣዩ በጀት ዓመት ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡ በተጨማሪም የኢትዮጵያ ሂሣብ ባለሙያዎች ማሠልጠኛ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ቀርቧል፡፡ እንዲሁም ዓለም አቀፍ የፐብሊክ ሴክተር የሂሳብ አያያዝ ደረጃዎች (IPSAS) ትግበራን በበላይነት የሚመራ

የሚኒስትሮች ስትሪንግ ኮሚቴ ተቋቁሞ ቀጣይ ስራዎችን ለማከናወን ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል፡፡ በሌላ በኩል ዜጎች ስለሀገራዊ በጀት ዝግጅት ሂደትና መረጃ አውቀውና ተረድተው በበጀት ትግበራ ሂደት ላይ በባለቤትነት እንዲሳተፉና እንዲቆጣጠሩ ለማድረግ በህግ አውጭው አካል ለ2015 በጀት ዓመት የፀደቀውን በጀት ለሁሉም ዜጎች በቀላልና ሊገባ በሚችል መልኩ አዘጋጅቶ ለማሠረጨት በታቀደው መሠረት የዜጎች የበጀት መረጃ ሠነድ (Citizens Budget) ተዘጋጅቶ መረጃው ተሰራጭቷል፡፡ እንዲሁም የኢትዮጵያ የበጀት ስርዓት ግልፅነት ደረጃን ለመለካት የሚያስችል 2ኛ ዙር የዳሰሳ ጥናት በዓለም አቀፍ የበጀት አጋርነት ድርጅት ተካሄዶ ውጤቱ እየተጠበቀ ይገኛል፡፡ ይህም ያለብንን ክፍተት በመለየት ማሻሻያዎችን በመቅረጽ ተግበራዊ ለማድረግ የሚረዳ ይሆናል፡፡

የገንዘብ እና የፋይናንስ ዘርፉን ለማዘመን በተወሰዱ የማሻሻያ እርምጃዎች፣ በሥራ ላይ ያሉ የገንዘብ ፖሊሲ ማስፈጸሚያ መሳሪያዎችን ለማጠናከርና አዳዲስ መሳሪያዎችን ሥራ ላይ ለማዋል ያስቻለ ከመሆኑም በላይ የፋይናንስ ዘርፉ ጉልህ ዕድገት እንዲያሳይና የፋይናንስ አካታችነት (financial inclusion) እንዲሻሻል አድርጓል፡፡ በመሆኑም የፋይናንስ አካታችነት መለኪያዎች ከፍተኛ መሻሻል እያሳዩ ሲሆን፣ የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎት ለዚህ መስፋፋት ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የትሬዠሪ ቢል ገበያው እንዲጠናከር ተደርጓል፣ የባንኮች የተቀማጭና የብድር ገንዘብ ከፍተኛ ጭማሪ አሳይቷል፣ የዲጂታልና የሞባይል ገንዘብ የፋይናንስ አገልግሎት በከፍተኛ ደረጃ ተስፋፍቷል፣ የተንቀሳቃሽ ንብረት ዋስትና መብት ተፈቅዶ በሥራ ላይ ለማዋል እንቅስቃሴዎች ተጀምረዋል፣ እንዲሁም በሸሪዓ ላይ የተመሠረቱ የፋይናንስ አገልግለቶች አገልግሎቶች በከፍተኛ ፍጥነት እየተስፋፉ ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ በተጨማሪም የካፒታል ገበያ ሥርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ በርካታ ሥራዎች እየተከናወኑ የሚገኙ ሲሆን፣ የግሉን ዘርፍ የፋይናንስ አቅርቦት ለማሻሻል የሚያስችሉ እርምጃዎችም ተግባራዊ በመደረጋቸው ተጨባጭ ለውጦች ተገኝተዋል፡፡

በኢንቨስትመንትና ንግድ ዘርፎች ተግባራዊ የተደረጉ ማሻሻያዎች የኢንቨስትመንትን ማዕቀፍ ለማዘመን የረዱ ከመሆናቸውም ባሻገር በኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ ሥራን ለማከናወን የሚወስደውን ጊዜና ወጪ ለመቀነስ አስችሏል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ኢንቨስትመንትን በመሳብና በመንከባከብ የኢንቨስትመንት አካባቢን ዘመናዊ የማድረግ ዓላማ ያለው አዲስ የኢንስትመንት ህግ ጸድቆ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡ እንዲሁም፣ የንግድ አገልግሎት ለማግኘት የሚያስፈልገውን ጊዜና ወጪ ለመቀነስ ያስቻሉ ከ80 በላይ የህግና አስተዳደር ማሻሻያዎች ተግባራዊ የተደረጉ ሲሆን፣ የአንድ መስኮት የኤሌክትሮኒክ ፖርታል አገልግሎትን ተግባራዊ ማድረግ በመቻሉ የንግድ ክሊራንስ አገልግሎት ለመስጠት ይወስድ የነበረውን አማካይ ጊዜ ከ44 ቀናት ወደ 13 ቀናት መቀነስ ተችሏል፡፡ ከነዚህም በተጨማሪ ከ1950ዎቹ ጀምሮ ሥራ ላይ የነበረውን የንግድ ህግ የዓለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎችን በማካተት አዲስ ዘመናዊ ህግ ጸድቆ ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ በአጠቃላይ በነዚህ ዘርፎች ቁልፍ የሆኑ የፖሊሲና መዋቅራዊ ማሻሻያዎችን ተግባራዊ በማድረግ የኢንስትመንትና የንግድ ማነቆዎችን ማስወገድ የተቻለ ሲሆን፣ የዘርፎቹን አፈጻጸም የበለጠ ውጤታማ እና ቀልጣፋ ለማድረግ የአገልግሎት ማሻሻያዎቹ በቀጣይም በጥልቀት እየተፈተሹ ተግባራዊ እንደሚደረጉ ይጠበቃል፡፡

የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ትግበራው በሎጀስቲክስ ዘርፉ ወጪ እንዲቀንስና የተሻለ ቅልጥፍና እንዲኖር ለማድረግ ተጨባጭ እርምጃዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ አድርጓል፡፡ በዚህም በዘርፉ በርካታ የንዑስ ዘርፍ ሎጀስቲክ አገልግሎቶች ለግልና ለውጭ ኢንቨስትመንት ተከፍተዋል፣ የደረቅ ወደቦች ግንባታ፣ ኦፕሬሽንና ማኔጅመንት ለውድድር ክፍት ተደርገዋል፡፡ በመሆኑም የጉምሩክ የወደብ ክሊራንስ፣ የጭነት መቆጣጠሪያዎችና የአገልግሎት ጥራትን ጨምሮ የዘርፉን አፈጻጸም ለመለካት የተቀመጡ የአፈጻጸም አመልካቾች መሻሻል አሳይተዋል፡፡ ከጥቂት ዓመታት በፊት ሥራ የጀመረው ዘመናዊ የኢትዮ-ጅቡቲ ባቡር አገልግሎትም በሎጀስቲክ ዘርፉ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል፡፡

በግብርናው ዘርፍ ረገድ ተግባራዊ የተደረጉ ማሻሻያዎች የሀገሪቱን እምቅ አቅም ለመጠቀም የሚያስችል አቅምን ለመፍጠር መሠረት የጣለ ሲሆን፣ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ ኤክስፖርትን ለማሳደግና ከውጭ ሲገባ የነበረውን የምግብ አቅርቦት በሀገር ውስጥ ምርት መተካት ያስቻለ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም በግብርናው ዘርፍ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ለማሳደግና ተወዳዳሪነትን ለማረጋጋጥ የግብርና ግብዓት ገበያው የሚመራበት የህግ ማዕቀፍ ተከልሷል፣ በርካታ የግብርና መካናይዜሽን መሳሪያዎችና ግብዓቶች ከቀረጥ ነጻ የሚገቡበት ሥርዓት ተዘርግቷል፣ የአረንጓዴ አሻራ ፕሮግራም ተግባራዊነት ህብረተሰቡ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርትን በማምረት ሥራ ላይ እንዲሳተፍ ሰፊ ንቅናቄን ከመፍጠሩም በላይ የሀገሪቱን እምቅ አቅም ለማልማት ዕገዛ እያደረገ ነው፡፡

የማዕድን ዘርፉን ዕምቅ አቅም በተሻለ ለመጠቀም የማዕድንና የፔትሮሊየም ኢንዱስትሪዎችን ለማሻሻል አስፈላጊ የሆኑ የህግና የፖሊሲ ማዕቀፍ ማሻሻያዎችም የተደረጉ ሲሆን፣ የዲጂታል የማዕድን ፈቃድና የኢንቨስትመንት ማኔጅመንት ሥርዓት ሥራ ላይ ውሏል፣ በማዕድን ዘርፉ በህጋዊ ሥርዓት መንቀሳቀስን ለማረጋገጥ በዘርፉ የሚሳተፉ ባህላዊ አምራቾች (artisanal) እና የጥቃቅንና አነስተኛ አምራቾች የሚመሩበት የሀገር ዓቀፍ የማዕድን ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ ውሏል፡፡ እንዲሁም የድንጋይ ከሰል የመሳሰሉ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ኢምፖርት በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት ጥረቶች እየተረጉ ሲሆን፣ ትልልቅ የማዕድን ካምፓኒዎች በዘርፉ በማዕድን ሥራ ላይ እንዲሰማሩ ኢንስትመንትን የማስተዋወቅ ሥራዎች እየተካሄዱ ነው፡፡ ይህም ዘርፉ የኤክስፖርትን ገቢ ለማሳደግና ለኢምፖርት የሚወጣውን ወጪ በመቀነስ ረገድ የሚኖረውን አስተዋጽኦ እንደሚያሳድግ ይጠበቃል፡፡

በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ የዲጂታል ኢኮኖሚን እምቅ አቅም ለኢኮኖሚ ዕድገት ምንጭነት ለመጠቀም የፖሊሲና ስትራቴጂ መሠረቶችን ለመዘርጋት የሚያስችሉ ማሻሻያዎች በዘርፉ ተግባራዊ የተደረጉ ሲሆን፣ የተቀናጀ ብሔራዊ ዲጂታል ስትራቴጂ ተቀርጾ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፣ እንዲሁም የዲጂታል

ልውውጥን፣ የኤሌክትሮኒክ ንግድንና የዲጂታል መንግስታዊ አገልግለቶችን ለማበረታታት የሚያስችሉ የተለያዩ የህግ ማዕቀፎችና ፖሊሲዎች ተግባራዊ እየተደረጉ ነው፡፡ እነዚህም ዜጎች የንግድ እንቅስቃሴዎችንና መንግስታዊ አገልግሎቶችን በዲጂታል ሥርዓት በሰፊው እንዲጠቀሙ ከማስቻሉም ባሻገር የኢኮኖሚ ዕድገቱን ለማፋጠን ከፍተኛ ዕገዛ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

## የተከበሩ አፈ ጉባኤ
## የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት

የአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያውን ተግበራዊ ለማድረግ መንግስት በቁርጠኝነት በወሰዳቸው እርምጃዎች ከዚህ በላይ ከተጠቀሱትም ውጭ የተገኙ በርካታ አዎንታዊ ውጤቶችን መጥቀስ የሚቻል ቢሆንም የቀረቡት ለግንዛቤ በቂ ናቸው የሚል ዕምነት አለኝ፡፡ ሆኖም ባለፉት ዓመታት ለሪፎርም ትግበራው ተግዳሮት የነበሩና በቀጣይ ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን ማንሳት ተገቢ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ባለፉት ዓመታት የኮቪድ-19 ወረርሽኝ፣ የአንበጣ መንጋ፣ የጎርፍና የድርቅ አደጋዎች፣ የአገር ውስጥ ግጭቶች እና ጦርነት፣ እንዲሁም የዓለም የመሠረታዊ ሸቀጦች ዋጋ መናር የሪፎርም ትግበራውን በማስተጓጎል ለኢኮኖሚው ተግዳሮቶችን ያስከተሉ እንቅፋቶች ነበሩ፡፡ እነዚህም የሪፎርም ትግበራው ከዚህም በላይ ስኬት እንዳያስመዘግብ የራሳቸውን ሚና ተጫውተዋል፡፡ በመሆኑም በቀጣዩ የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ እነዚህን የኢኮኖሚ ተግዳሮቶች ለመቅረፍ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል፡፡

## የተከበሩ አፈ ጉባኤ
## የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት

ከእነዚህ ተግዳሮቶች መካከል በቀጣይ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራበት ጉዳይ በፊስካል ዘርፉ ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ የሚሰሩ ተግበራትን የሚመለከት ነው፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ኢኮኖሚው ሊያመነጨው የሚችለውን የመንግስትን የአገር ውስጥ ገቢ እምቅ አቅም አሟጦ ለመሰብሰብ የሚያስችሉ ማሻሻያዎችን ተግባራዊ በማድረግ የልማት ፋይናንስ ፍላጎቶቻችንን በራሳችን የመሸፈን አቅማችንን በማሳደግ እና

የመንግስትን የፊስካል ጉድለት ጤናማ በማድረግ ላይ ትኩረት ተደርጎ መስራት ተገቢ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ባለፉት ዓመታት የታክስ ገቢና የውጭ ዕርዳታና ብድር አሰባሰብ ዝቅተኛ አፈጻጸም በማሳየታቸው የተያዘውን የገቢ ዕቅድ ማሳካት አልተቻልም፡፡ በተመሳሳይም ከልማት አጋሮች የሚጠበቀው የልማት ድጋፍ በከፍተኛ ደረጃ የቀነሰ ሲሆን፣ በበጀት ድጋፍ መልክ ይገኛል ተብሎ የተያዘው ዕቅድ ሙሉ ለሙሉ ሳይገኝ ቀርቷል፡፡ በአንጻሩ ደግሞ የተከሰቱት አደጋዎች የመንግስት ወጪ ፍላጎት እጅግ እንዲጎር ያደረጉ ሲሆን፣ እነዚህን ተጨማሪ የሰብዓዊ ድጋፍ፣ የህግ ማስከበርና የዕዳ ክፍያ እና የዐፈር ማዳበሪያ ድጎማ ተጨማሪ ወጪዎች ለመሸፈን በተወሰነ ደረጃ በበጀት ታቅደው የነበሩ የልማት ወጪዎችን ማሸጋሸግ ከመጠየቁም በላይ የገጠመንን ተጨማሪ የበጀት ጉድለት ከሀገር ውስጥ ተጨማሪ ብድር በመውሰድ መሸፈን የግድ ሆኗል፡፡ እንዲሁም በሀገር በቀል ማሻሻያው የአጠቃላይ የመንግስት የውጭ ዕዳ ስጋት ደረጃን ወደ መካከለኛ ስጋት ደረጃ ለመቀነስ የተደረጉት የዕዳ ሽግሽግ ስምምነት ጥረቶች የተወሰኑ ስኬቶች ቢያስገኙም፣ በተለይ በዕዳ ስጋት ቅነሳው ላይ ትርጉም ያለው ለውጥ ያመጣል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት የG20 Common Framework ዕድል በተፈለገው ፍጥነት ተግባራዊ ባለመደረጉ እና በመዘግየቱ ቀጣይ የቤት ሥራ ሆኗል፡፡

ሌላውና በቀጣይ ትኩረት የሚሻው የኢኮኖሚው ተግዳሮት የዋጋ ንረት ሲሆን፣ በሪፎርም ትግበራ ዘመን ውስጥ የዋጋ ንረት ለረዥም ወራት ከ30 በመቶ በላይ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ለዋጋ ንረቱ እንደ መንስኤ የሚታዩ ጉዳዮች በርካታ ሲሆኑ፣ የምርትና ምርታማነት በበቂ ሁኔታ አለመጠናከር፣ የአገር ውስጥ የንግድ ሰንሰለት፣ የፊሲካል ጉድለት አሸፋፈን እና የዓለም ዓቀፍ ሸቀጦች ዋጋ ዕድገት ተጽእኖ በዋናነት የሚጠቀሱ ምክንቶች ናቸው፡፡ የዋጋ ንረት የሸማቹን የመግዛት አቅም የሚያዳክም ከመሆኑም በላይ በረዥም ጊዜ የኢኮኖሚውን አፈጻጸም እጅጉን የሚጎዳ በመሆኑ ቀጣይነት ያለው እርምጃ ተወስዶ መስተካከል የሚገባው የኢኮኖሚ ተግዳሮት ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ መንግስት ለጊዜውም ቢሆን ዝቅተኛ ገቢ ያለው ህብረተሰብ ላይ ያለውን ጫና ለማርገብ እንዲረዳ የመሠረታዊ ምግብ ሸቀጦች አቅርቦት እንዲሻሻል ቀረጥና ታክስ

ሳይከፈልባቸው እንዲገቡ በማድረግ እና የማዳበሪያ ዋጋን በድጎማ ለማቅረብ እንዲቻል በጀት በመመደብ ችግሩ እንዲቃለል ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡ በቀጣይም የዋጋ ንረትን በማረጋጋት የኑሮ ውድነትን ለመቅረፍ የተጀመሩ ምርታማነትን ሊያሳድጉ የሚችሉ ማሻሻያዎችን እና ሌሎች የዋጋ ንረትን ሊያረጋጉ የሚችሉ እርምጃዎችን መውሰድ ተገቢ ይሆናል፡፡

እንዲሁም የውጭ የኢኮኖሚ ዘርፍ (Balance of Payment) በእነዚህ በተከሰቱት አደጋዎች ከፍተኛ ተጽእኖ የደረሰበት ሌላው ሲሆን፣ የኤክስፖርት ገቢያችን አሁን ከተገኘው አፈጻጸም በላይ እንዳይሆን ከማድረጉም በላይ፣ የኢምፖርት ዕቃዎች፣ በተለይም የማዳበሪያና የነዳጅ እንዲሁም የመንግስት ዕዳ ክፍያ ወጪዎች እንዲጨምር ያደረገ ሲሆን፣ በአንጻሩ ደግሞ የልማት አጋሮች ለኢትዮጵያ የሚሰጡትን ድጋፍ በመቀነሳቸውና የቀጥታ በጀት ድጋፍ በማቆማቸው የውጭ ኦፊሲያል ፍሰት (official transfer) በከፍተኛ ደረጃ እንዲቀንስ አድርጓል፡፡ ይህም የሀገሪቱ የውጭ ክፍያ ሚዛን እንዲሰፋ ምክንያት ሆኗል፡፡ በመሆኑም የክፍያ ሚዛን ጉድለትን ለማጥበብና የውጭ ምንዛሬ አቅርቦትን ለማሻሻል በቀጣይ ሰላማችንን በማጽናት የምርታማነት፣ የፕሮሞሽንና የዲፕሎማሲ ሥራዎችን በማከናወን የውጭ ካፒታል ፍሰት እንዲጨምር ትኩረት አድርጎ መስራት ተገቢ ነው፡፡

**የተከበሩ አፈ ጉባኤ**
**የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት**

እነዚህን የገጠሙንን የኢኮኖሚ ተግዳሮቶች ለመፍታትና በመጀመሪያው የአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ እስከአሁን ተግባራዊ ያልተደረጉ እና አዳዲስ ማሻሻያዎችን አጠናክሮ ተግባራዊ ለማድረግና የኢኮኖሚ ዕድገቱን ለማስቀጠል የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ሁለተኛው ምዕራፍ ረቂቅ የተዘጋጀ ሲሆን፣ ምክክር እየተደረገበት ይገኛል፡፡ በዚህም የገጠሙንን ተግዳሮቶች ለመፍታት የሚያስችሉ የማክሮ ኢኮኖሚ፣ የፊስካል እና ፋይናንሻል ፖሊሲዎች እና የኢንስትመንትና የንግድ አካባቢዎችን ምቹ ለማድረግ እንዲሁም የዘርፎችን ምርታማነት እና ተወዳዳሪነት ለመጨመር የሚያስችሉ መጠነ

ስራ ማሻሻያዎች ተግበራዊ የሚደረጉ ይሆናሉ፡፡ ይህ የቀረበው የቀጣዩ በጀት ዓመት ረቂቅ በጀትም እነዚህን የኢኮኖሚ ሪፎርሞች እና በእነዚህ ላይ በመመሥረት የተዘጋጁ የቀጣዩ በጀት ዓመት ማክሮ ኢኮኖሚ ትንበያዎችን ታሳቢ በማድረግ የተዘጋጀ ነው፡፡

ረቂቅ በጀቱ የተዘጋጀው የተቀመጡ ዋና ዋና የፊሲካል ግቦችን፣ በጀቱ ቅድሚያ ትኩረት የሚያደርግባቸውን የገቢ እና የወጪ ፖሊሲ አቅጣጫዎችን፣ ወቅታዊ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታን እና የፊሲካል አቅምን ባገናዘበ መልኩ ነው፡፡ እነዚህ በሁለተኛው ምዕራፍ የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ውስጥ የተካተቱ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ተግበራዊ ሲደረጉ በቀጣዮቹ ዓመታት የማክሮ ኢኮኖሚው መሻሻል እንደሚያሳይ ታሳቢ የተደረገ ሲሆን፣ የመንግስት የፊሲካል ተግዳሮቶችም በየደረጃው እየተቀረፉና ትኩረቱ በልማት ላይ እንደሚሆን ከፍተኛ ግምት ተወስዷል፡፡ በተለይም በቀጣይ ዓመታት የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚን ማረጋገጥና ይህም የኢኮኖሚ ዕድገት እንዲመዘገብ አስቻይ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ለማድረግ በማሻሻያው እንደ ግብ የተያዘ ነው፡፡ ለዚህም የመንግስት ገቢ አሰባሰብን ለማሻሻል፣ ብቁና የግል ዘርፉን ተሳትፎ ለማረጋገጥ የሚረዳ የፐብሊክ ኢንስትመንት እንዲኖር ለማድረግ፣ የመንግስትን ዕዳ ስጋት ደረጃ ለመቀነስ፣ የውጭ ምንዛሬ ፍላጎትን ለማሟላት እና የፋይናንስ አቅርቦትን ለማሻሻል የሚያስችሉ በርካታ ተግባራት ለማከናወን ታቅዷል፡፡

የመንግስት ገቢ አሰባሰብን ለማሻሻል ግብር ከፋይ ተኮር እና ውጤታማ የታክስ አስተዳደር ሥርዓት ለመዘርጋት የሚያስችሉ ተግበራትን ለማከናወን የታቀደ ሲሆን፣ አካታች የኢኮኖሚ ዕድገትን እና የታክስ ገቢ አሰባሰብን የሚደግፉ የታክስ ፖሊሲዎችና ህጎችም ተግበራዊ ይሆናሉ፡፡ በዚህም የታክስ አስተዳደር አገልግሎቱ ከግብር ከፋዩ ጋር የሚኖርን የማህበራዊ ውል (social contract) ማዕከል ያደረገ ደንበኛን የማገልገል ባህል እንዲዳብር የሚያደርግ ሥርዓት እንዲዘረጋ የሚያደርግ አገልግሎት እንዲኖር ማስቻል ሲሆን፣ ግልጽና ቀላል የታክስ አስተዳደር እንዲኖር፣ ሥርዓቱ በዲጂታላይዜሽን እንዲታገዝ የማድረግ፣ ውጤታማ የታክስ ኦዲት እንዲዘረጋ የማድረግና የታክስ ማበረታቻ ለታለመለት ዓላማ መዋሉንና ዓላማውን ማሳካቱ

የሚገመገምበት ሥርዓትን መዘርጋት ይሆናል፡፡ ለዚህም በገቢ አሰባሰቡ እመርታ እንዲኖርና የኢኮኖሚ ዕድገቱን በመደገፍ እንዲሁም የታክስ መሠረትን በማስፋት፣ ፍትሀዊነትን በማረጋገጥና በአፈጻጸም ላይ የተመሠረተ የማበረታቻ ሥርዓት ላይ ያተኮረ የመካከለኛ ዘመን የገቢ ስትራቴጂ (Medium-Term Revenue Strategy-MTRS) ተቀርጾ ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል የመንግስት ኢንቨስትመንት ትኩረት ልማትን የሚያረጋግጥና የኢኮኖሚ ዕድገትን የሚያፋጥን፣ የግል ኢንቨስትመንትን ለማሳለጥ የሚረዳ፣ እንዲሁም የመንግስት ልማት ድርጅቶች ማሻሻያ ተጠናክሮ ተግበራዊ እንዲሆን በማድረግ ተወዳዳሪነትንና ውጤታማነት የሚያረጋግጥ እንዲሆን የሚያስችሉ ማሻሻያዎች ተግባራዊ የሚደረጉ ይሆናል፡፡ በዚህም የካፒታልና የመደበኛ ወጪዎችን በማመጣጠን ለልማትና ዕድገት አስተዋጽኦ ለሚያደርጉ ዘርፎች ወጪዎች ትኩረት መስጠት፣ የፐብሊክ ኢንስትመንት ውጤታማነትን ለማሻሻል የሚያስችሉ የፐብሊክ ኢንቨስትመንት ማኔጅመንት መሳሪያዎችን በተጠናከረ ሁኔታ ተግበራዊ ማድረግ፣ እና የመንግስት ግዥ እና ሪፖርት ሥርዓት በዲጂታል ቴክኖሎጂ የታገዘ እንዲሆን ማድረግን ባካተተ መልክ የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ማሻሻያዎችን በተጠናከረ መንገድ ተግባራዊ ማድረግ የመሳሰሉ በርካታ ተግባራት ሥራ ላይ የሚውሉ ይሆናሉ፡፡ በተጨማሪ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ስትራቴጂያዊ የመንግስት ኢንቨስትመንት ክንድ እንዲሆን ማጠናከር፣ የመንግስትና የግል አጋርነት የግል ዘርፉን ኢንቨስትመንት የበለጠ ለማሳለጥ እንዲያስችል ማጠናከር እና ሌሎች የመንግስት የልማት ድርጅቶች ማሻሻያዎች ተግበራዊ የሚደረጉ ይሆናል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በንግድና ኢንቨስትመንት የገበያን ተደራሽነትና ተወዳዳሪነት ለማሻሻል፣ የመካከለኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞችን ዕድገት ለማፋጠን፣ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ፍሰትንና አስተዋጽኦውን ለማሻሻል፣ እና የተቀላጠፈ የሠራተኛ-አሰሪ የክርክር ጉዳዮች አሰጣጥ እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችሉ ማሻሻያዎችን፣ እንዲሁም የኢኮኖሚ ዕድገቱን ለማፋጠን ወሳኝ የሆኑ ዘርፎችን

ምርታማነትና ተወዳዳሪነት ለማሳደግ የሚያበቁ በሪፎርም ፕሮግራሙ የታቀዱ በርካታ ማሻሻያዎች ተግባራዊ የሚደረጉ ይሆናል፡፡

በተጨማሪም የማሻሻያ ዕቅዱን በብቃትና በስኬታማነት ተግባራዊ ለማድረግ የሚቻለው የመንግስትን የመፈጸም አቅም በማጎልበት በመሆኑ፣ ብቁና ውጤታማ የሲል ሰርቪስ ተቋማት እና አደረጃጀት እንዲኖር ለማድረግ እንዲሁም የተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ መረጃ አያያዝና ብልሹ አሰራርን ለማስወገድ እና ውጤታማና ዘመናዊ አገልግሎትን ለመስጠት የሚያስችሉ ማሻሻያዎች ተግበራዊ ይደረጋሉ፡፡ የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርሙ በፌዴራል እና በክልል ተቋማት በተጠናከረና ባልተማከለ መንገድ ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን፣ የመንግስትን በጀት በውጤታማነት እና በቁጠባ ለመጠቀም ከፍተኛ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡

### የተከበሩ አፈ ጉባኤ
### የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት

ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ባለፉት ዓመታት መንግስት በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ የተካተቱ መጠነ ሰፊ የኢኮኖሚ ሪፎርም እርምጃዎችን ተግባራዊ በማድረጉ፣ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የተለያዩ ተጽእኖዎችን በመቋቋም ከ6 በመቶ በላይ አማካይ ዓመታዊ ዕድገት ማስመዝገብ እና ዕድገቱ ቀጣይ እንዲሆን ማድረግ ተችሏል፡፡ ይህም የግብርና ምርታማነትን ለማሻሻል፣ የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፉን ዕድገት ለመደገፍ በተደረጉ ከፍተኛ ጥረቶች የተገኘ ውጤት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የኤክስፖርት ገቢ ባለፉት ዓመታት ከፍተኛ መሻሻል የታየበት ሲሆን የውጭ ቀጥተኛ ኢንስትመንትም በአንጻራዊነት ዕድገት አሳይቷል፡፡ ሆኖም ባለፉት ዓመታት ሀገራችን ያጋጠሟት ዘርፈ-ብዙ ውስጣዊ እና ዓለም ዓቀፋዊ ተጽእኖዎች በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ጫናዎችን በማሳደራቸው በርካታ የኢኮኖሚ ተግዳሮቶች ተከስተዋል፡፡ በተለይም የተከሰቱት ቀውሶች በፊሲካል ላይ ያስከተሉትን ተጽእኖ ለማስተካከል ዓመታትን መፍጀቱ የማይቀር በመሆኑ፣ የመንግስት በጀት በአጭርና በመካከለኛ ጊዜ ሊከተል የሚገባውን ትኩረት በጥንቃቄ በማየት መወሰን ተገቢ ይሆናል፡፡ ይህ ረቂቅ

ዓመታዊ በጀትም ሲዘጋጅ፣ ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡ የሪፎርም ዕቅዶች ተግባራዊነትን መሰረት በማድረግ በማክሮ ኢኮኖሚ ረገድ ታሳቢ የተደረጉ ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

የኢኮኖሚ ዕድገቱን ቀጣይ ከማድረግ አንጻር በቀጣዮቹ ዓመታት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከገጠሙት ቀውሶች ተላቆ ሙሉ ለሙሉ ጤናማ አቋም ላይ እንደሚደርስ ታሳቢ የተደረገ ሲሆን፣ በያዝነው በጀት ዓመት ኢኮኖሚው ከገጠሙት ቀውሶች በተወሰነ ደረጃ ተጽኦናው ረገብ በማለቱና በመንግስት በኩልም ኢኮኖሚው እንዲያንሰራራ እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች የተሻለ ዕድል እንደሚፈጥሩ ታሳቢ በማድረግ፣ ኢኮኖሚው ከነበረው ችግር በማገገም የ7.5 በመቶ ዕድገት እንደሚያስመዘግብ ተገምቷል፡፡ እንዲሁም፣ በ2016 በጀት ዓመት የ7.9 በመቶ ዕድገት እንደሚመዘገብ ትንበያ የተደረገ ሲሆን፣ የአጠቃላይ ዋጋ ዕድገት የተወሰነ ቅናሽ እንደሚያሳይና ባለሁለት አሃዝ ሆኖ እንደሚቀጥል ግምት ተወስዷል፡፡

የገቢ ዕቃዎች ዋጋ (Value of goods import) በ2015 በጀት ዓመት የ7.2 በመቶ ዕድገት እንደሚያሳይ የተገመተ ሲሆን፣ በ2016 የ18.9 በመቶ ዕድገት እንደሚኖረው ታሳቢ ተደርጓል፡፡ ከገንዘብ ፖሊሲ አንጻር በመካከለኛ ዘመን ውስጥ ጥብቅ የገንዘብ ፖሊሲ ተግባራዊ እንደሚደረግ፣ የገንዘብ አቅርቦትን በመገደብ አሁን የሚታየውን ከፍተኛ የዋጋ ንረት ለማረጋጋት ጥረት እንደሚደረግ፣ ለበጀት ጉድለት መሸፈኛ ከብሔራዊ ባንክ በቀጥታ የሚወሰደው ብድር ከፍተኛ ቅናሽ እንደሚያሳይ፣ ባለፉት ዓመታት በተለያዩ የገንዘብ ብድር ዘዴዎች (monetary instruments) ወደ ኢኮኖሚው ውስጥ የተሰራጨውን ገንዘብ መልሶ ለመሰብሰብ በገንዘብ ፖሊሲው እርምጃ እንደሚወሰድ (liquidity mopping up)፣ እንዲሁም በአጠቃላይ ተገቢ የሆነ የገንዘብ አቅርቦት (broad money) ዕድገት እንዲኖር እንደሚደረግ ታሳቢ ተደርጓል፡፡

በፊሲካል ፖሊሲ ረገድ፣ የታክስ ገቢ አሰባሰብ እመርታዊ ለውጥ እንዲያመጣ የሚያስችሉ የታክስ ፖሊሲ ማለትም፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሻሻያ፣ የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ማሻሻያ፣ የኤክሳይዝ ቴምብር፣ እና የማህበራዊ ዋስትና ልማት ቀረጥ

(social welfare development duty) የመሳሰሉ የታክስ ህጎችን ተግባራዊ የሚደረጉ ይሆናል፡፡ እንዲሁም በታክስ አስተዳደሩ ረገድም ትርጉም ያለው ለውጥ ለማምጣት የሚያስችሉ ማሻሻያዎች ተግባራዊ የሚደረጉ ሲሆን፣ በተለይም የገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች የሰው ሀይልና ተቋማዊ አቅምና የአሠራር ችግሮችን እና አደረጃጀቱን በጥልቀት በመፈተሽ አስፈላጊ የሆኑ ማሻሻያዎች ተግባራዊ የሚደረጉ ይሆናል፡፡ ለዚህም በተግባር ተጨባጭ ለውጥ እንዲመጣ በመንግስት በኩል አስፈላጊው ድጋፍ ሁሉ እንደሚደረግ ታሳቢ ተደርጓል፡፡ ከታክስ ገቢ በተጨማሪም ታክስ ካልሆኑ ምንጮች የሚሰበሰቡት ገቢዎች አቅምን አሟጦ ለመጠቀም በሚያስችል መልክ በዝርዝር በማየት በገቢ ዕቅዱ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም በዕርዳታ እና ብድር መልክ ከልማት አጋሮች የሚገኘው ሀብት በመጠኑም ቢሆን እንዲካተት ተደርጓል፡፡

በወጪ ረገድ፣ አሁን ካለው ከፍተኛ የፋይናንስ እጥረት አኳያ የተጀመሩ ፕሮጀክቶችን ለማስጨረስ፣ ለዕዳ ክፍያ፣ በጦርነቱ የወደሙ መሠረተ ልማቶችና አገልግሎቶች ወደ ቀድሞ ይዞታቸው መልሶ ለማቋቋምና ለዕለት ዕርዳታ፣ ለአፈር ማዳበሪያ ድጎማ እንዲሁም ለብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት የበጀት ድጋፍ ቅድሚያ ትኩረት ተሰጥቷል፡፡ በተለይም አሁን ያለው የፋይናንስ እጥረት ሁሉንም የወጪ ፍላጎቶቻችንን በማዕቀፉ ለማካተት የማያስችል በመሆኑ የተጀመሩ የካፒታል ፕሮጀክቶችም ቢሆኑ፣ የክፍያ ጊዜያቸውን በማሸጋሸግ የወጪ በጀት ቅነሳ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ጭምር ታሳቢ በማድረግ የተዘጋጀ ረቂቅ በጀት መሆኑን ለማስገንዘብ እፈልጋለሁ፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ የ2016 በጀት ዓመት የመደበኛ ወጪ ጣሪያን ለመወሰን በሰሜኑ ጦርነት ረገድ የተደረሰውን የሰላም ስምምነት መሰረት በማድረግ ለሀገር መከላከያ የሚያስፈልገው ወጪ ባለፈው በጀት ዓመት ከነበረው አንጻር በመጠኑ ዝቅ እንዲል በማድረግ፣ በጦርነቱ እና በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ለተጎዱ ዜጎች የዕለት ዕርዳታ ለማቅረብ እና ለልማታዊ ሴፍቲኔት የሚያስፈልገውን ወጪ፣ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ የመጣውን የአገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር ዕዳ ክፍያም ታሳቢ በማድረግ የተዘጋጀ ነው፡፡ የካፒታል ወጪ ፍላጎትን በተመለከተ በመካሄድ ላይ ላሉ

ነባር ፕሮጀክቶች አሁን ያለውን ዕቅድ ከማሳካትና እንዲጠናቀቁ ከማድረግ አንፃር ቅድሚያ የተሰጠ ቢሆንም በቀጣይ በጀት ዓመት አዳዲስ የካፒታል ፕሮጀክቶች በበጀት ማካተት እንደማይቻልና በተወሰነ ደረጃ የነባር ፕሮጀክቶችንም የክፍያ ጊዜን በማራዘም ወጪው እንዲሸጋሸግ በማድረግ፣ በጦርነቱ የወደሙ መሠረተ ልማቶችና አገልግሎቶች ወደ ቀድሞው ይዞታቸው ለመመለስ የመልሶ ማቋቋም ስራን ታሳቢ በማድረግ የተዘጋጀ ነዉ፡፡ ለ2016 የተያዘው የፌዴራል መንግስት የመደበኛና የካፒታል በጀት ካለው የፊሲካል ጫና አንጻር ቅናሽ እንዲኖረው ቢደረግም ለብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሚመደበው የበጀት ድጋፍ ግን በተቻለ መጠን በነበረበት እንዲቆይ ለማድረግ ተችሏል፡፡ በመሆኑም የክልሎች የበጀት ድጋፍ አመዳደብ የፌዴራል መንግስት ያለውን ሀብት መጠንና የፌዴራል መንግስት የግዴታ ወጪዎችና የበጀት ጫናን ግምት ውስጥ በማስገባት፣ ክልሎች ከ2013 በጀት ዓመት ጀምሮ ተግባራዊ ከተደረገው የጋራ ገቢ ቀመር ማሻሻያ ከፍተኛ ተጠቃሚ መሆናቸውንና ይህ በአንጻሩ ደግሞ የፌዴራል መንግስትን የገቢ ቋት በእጅጉ የቀነሰ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ እና አዲሱ የንብረት ግብርም ተጨማሪ የገቢ አቅም እንደሚፈጥርላቸው ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡ በሌላ በኩል ለክልሎች የሚደረገው የዘላቂ ልማት ግቦች ድጋፍ የተጀመሩ የአግሮ ኢንዱስትሪ ግንባታዎችን ለማጠናቀቅና በአነስተኛ መስኖ ስራዎች ድጋፍ ላይ ብቻ እንዲያተኩር ታሳቢ በማድረግ የተመደበ ነው፡፡

በአጠቃላይ የ2016 በጀት ዓመት ረቂቅ የፌዴራል መንግስት በጀት ጤናማ የፊሲካል ሁኔታን የማረጋገጥ (Fiscal consolidation) አቅጣጫን ተከትሎ የተዘጋጀ ሲሆን፣ ከሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ሁለተኛው ምዕራፍ ዕቅድ ጋር ተጣጥሞ የተዘጋጀ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም የመንግስትን የፊሲካል አቅም ለማጠናከር የመንግስት የሀገር ውስጥ ገቢ አሰባሰብ ላይ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ መስራት አማራጭ የሌለው መሆኑን መገንዘብ ይገባል፡፡ እንዲሁም ሀገራችን በየጊዜው በሚገጥማት የተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት የሚከሰቱ ተጽእኖዎች የሚፈጥሩትን የፊሲካል ጫና በዕቅድና በተደራጀ መልክ ለመቀነስ የሚያግዙ ሥርዓቶችም ለመዘርጋት የተለያዩ ስራዎች

እየተከናወኑ ሲሆን፣ እነዚህንም ተግባራዊ በማድረግ የፊሲካል ሥርዓቱ እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም የመንግስት ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም ለማጠናከር የፐብሊክ ኢንቨስትመንት ዕቅድ ሥርዓት በተጠናከረ መንገድ ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል፡፡

**የተከበሩ አፈ ጉባኤ**
**የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት**

ከላይ በዝርዝር የቀረቡትን ዋና ዋና ታሳቢዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት አጠቃለይ የፌዴራል መንግሥት የ2016 በጀት ዓመት ረቂቅ በጀት በዝርዝር ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን፣ በጀቱንም ለማዘጋጀት ከባለበጀት መ/ቤቶች ጋር ሰፊ ውይይቶችና ምክክሮች ተደርጎበት በሚኒስትሮች ም/ቤት ተደግፎ የቀረበውን የፌዴራል መንግስት የገቢና የወጪ በጀት እንደሚከተለው በዝርዝር አቀርባለሁ፡፡

በገቢ ረገድ በ2016 በጀት ዓመት ጠቅላላ ገቢ የውጭ ዕርዳታን ጨምሮ ብር 520.6 ቢሊዮን እንደሚደርስ የተገመተ ሲሆን፣ ይህም በ2015 በጀት ዓመት ከነዚህ ምንጮች ይሰበሰባል ተብሎ ከተገመተው አንጻር የ27.7 በመቶ ጭማሪ አለው፡፡ ይህም ጠቅላላ ገቢ ብር 440.8 ቢሊዮን ከታክስ፣ ብር 38.7 ቢሊዮን ታክስ ካልሆኑ ምንጮች፣ እንዲሁም ብር 6.3 ቢሊዮን ከቀጥታ የበጀት ድጋፍ እና ብር 34.8 ቢሊዮን ከፕሮጀክቶች ዕርዳታ እንደሚገኝ የተገመተ ነው፡፡ ከዚህ ከታቀደው ጠቅላላ ገቢ ውስጥ 92.1 በመቶ የሚሆነው ድርሻ ከታክስ እና ታክስ ካልሆኑ የገቢ ምንጮች እንደሚገኝ የታቀደ ገቢ ነው፡፡ በሌላ በኩል ከታክስ ገቢ ለመሰብሰብ የታቀደው ብር 440.8 ቢሊዮን ገቢ የጠቅላላ የገቢና ዕርዳታው 84.7 በመቶ ድርሻ የያዘ ሲሆን፣ በ2015 ከታክስ ገቢ ይሰበሰባል ተብሎ ከታቀደው ብር 348 ቢሊዮን የገቢ ግምት አንጻር የ26.7 በመቶ ጭማሪ አለው፡፡ በሌላ በኩል ታክስ ካልሆኑ ምንጮች ለመሰብሰብ ከታቀደው ብር 38.7 ቢሊዮን ውስጥ ብር 20.8 ቢሊዮን (53.7 በመቶው) የሚሆነው ከመንግስት የልማት ድርጅቶች የትርፍ ድርሻ የሚገኝ ገቢ ነው፡፡ የውጭ ዕርዳታን በተመለከተ ለ2016 በጀት ዓመት ወጪ መሸፈኛ ብር 41.1 ቢሊዮን ከልማት አጋሮች እንደሚገኝ የታቀደ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ብር 6.3 ቢሊዮን በቀጥታ ወደ መንግስት ማዕከላዊ ግምጃ ቤት

የሚፈስ ሲሆን ቀሪው ብር 34.8 ቢሊዮን ደግሞ በቀጥታ ለተወሰኑ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ በዕርዳታ የሚገኝ ነው፡፡ ይህ በ2016 በጀት ዓመት ከውጭ ዕርዳታ እንደሚገኝ የታቀደው ገቢ በ2015 በጀት ዓመት ይገኛል ተብሎ ከተገመተው ገቢ አንጻር የ33.4 በመቶ ጭማሪ ሲሆን፣ ከጠቅላላ የ2016 የገቢና ዕርዳታ ዕቅድ 7.9 በመቶው ነው፡፡

**የተከበሩ አፈ ጉባኤ**
**የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት**

ከላይ በዝርዝር የቀረቡትን ዋና ዋና የወጪ ታሳቢዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የተዘጋጀው አጠቃላይ የፌዴራል መንግሥት የ2016 ጠቅላላ የወጪ በጀት ብር 801.65 ቢሊዮን ሲሆን ይህም ለ2015 ከጸደቀው የወጪ በጀት ጋር ሲነጻጸር የ1.9 በመቶ ዕድገት ያሳያል፡፡ ከዚሁ ጠቅላላ የወጪ በጀት ውስጥ ለፌዴራል መንግስት ለመደበኛ ወጪ ብር 370.14 ቢሊዮን፣ ለካፒታል ብር 203.44 ቢሊዮን እንዲሁም ለክልል መንግሥታት ድጋፍ ብር 214.07 ቢሊዮን እና ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ብር 14 ቢሊዮን ተደግፎ የቀረበ ነው፡፡

በአጠቃላይ ተደግፎ ከቀረበው ጠቅላላ ወጪ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው ለመደበኛ ወጪ የተመደበው ሲሆን፣ ይህም የጠቅላላ በጀቱ 46.2 በመቶው ነው፡፡ ይህም ለመደበኛ የተደለደለው በጀት ለ2015 ከጸደቀው መደበኛ በጀት አንጻር የ7.25 በመቶ ብልጫ አለው፡፡ ከዚህ ለመደበኛ ከተመደበው ወጪ በጀት ውስጥ 63.6 በመቶ የሚሆነው ከፍተኛው ድርሻ የተመደበው ለሀገር ውስጥና ለውጭ ዕዳ ክፍያ፣ ለማዳበሪያ ድጎማ የበጀት ድጋፍ፣ ለአደጋ መከላከል እና ለመጠባበቂያ የተደለደለ ነው፡፡ በአጠቃላይ የ2016 የመደበኛ በጀት በየመ/ቤቱ ያለውን አዲሱን አደረጃጀት ታሳቢ በማድረግ፣ የበጀት አጠቃቀም በቁጠባና በውጤታማነት ላይ ያተኮረ እንደሚሆን፣ እንዲሁም አዳዲስ የሠራተኛ ቅጥር እንደማይኖር ታሳቢ በማድረግ የተዘጋጀ መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡

በሌላ በኩል ለ2016 በጀት ዓመት ለፌዴራል መንግስት የካፒታል በጀት የተደለደለው ብር 203.44 ቢሊዮን በጀት የጠቅላላ ወጪ በጀቱ 25.4 በመቶ ሲሆን በ2015 ከተመደበው ጋር ሲነጻጸር የ6.7 በመቶ ቅናሽ ያሳያል፡፡ ይህም የካፒታል በጀት ወጪ አሸፋፈኑ ሲታይ ብር 146.1 ቢሊዮን ከመንግስት ግ/ቤት፣ ብር 31.6 ቢሊዮን ከፕሮጀክቶች ዕርዳታ እንዲሁም ብር 25.7 ቢሊዮን ከፕሮጀክቶች ብድር እንደሚሸፈን የተያዘ ነው፡፡ ከዚህ ለካፒታል ከተመደበው የወጪ በጀት ውስጥ 81.8 በመቶ የሚሆነው ለማህበራዊና ኢኮኖሚ ዘርፎች የተመደበ በጀት ሲሆን፣ ከጠቅላላ ካፒታል በጀት ውስጥ 68.7 በመቶ የሚሆነው የተመደበው ቅድሚያ ትኩረት ለተሰጣቸው የመንገድ፣ የትምህርት፣ የግብርናና ገጠር ልማት፣ የውሃና የጤና ዘርፎች ነባር ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ ነው፡፡ እንዲሁም በጦርነቱ ምክንያት የወደሙ ንብረቶች እና አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ወደ ነበሩበት መልሶ ለመገንባትና ለማቋቋም ለተጀመረው ፕሮጀክት ከመንግስት ግምጃ ቤት ብር 20.0 ቢሊዮን ተደግፎ ቀርቧል፡፡

በተጨማሪም ለ2016 በጀት ዓመት ለክልል መንግስታት የበጀት ድጋፍ ብር 214.07 ቢሊዮን የተደገፈ ሲሆን፣ ይህም ለ2015 ተመድቦ ከነበረው ብር 209.38 ቢሊዮን አንጻር የ2.24 በመቶ ጭማሪ አለው፡፡ ከዚህ ለክልሎች ከተመደበው በጀት ውስጥም ከመንግስት ግምጃ ቤት የሚሸፈነው ብር 205 ቢሊዮን ነው፡፡ እንዲሁም ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ድጋፍ ለክልሎች ለ2016 ብር 14.0 ቢሊዮን የተመደበ ሲሆን፣ ይህም ለአግሮ ፕሮሰሲንግ፣ ለስራ ዕድል ፈጠራ እንዲሁም በክልሎች ለሚካሄዱ ለአነስተኛ እና መካከለኛ መስኖ ልማት ካፒታል ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የሚውል ነው፡፡

### የተከበሩ አፈ ጉባኤ
### የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት

ከዚህ በላይ በዝርዝር ለማቅረብ እንደሞከርኩት በ2016 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት ከሀገር ውስጥ ገቢ እና ከውጭ አገር ዕርዳታ ምንጮች በድምሩ ብር 520.6 ቢሊዮን ገቢ ለመሰብሰብ የሚያስችል ዕቅድ ያዘጋጀ ሲሆን፣ ለመደበኛ፣ ለካፒታል እና

ለብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት የበጀት ድጋፍና የዘላቂ የልማት ግቦች ማጠናከሪያ ወጪ ጠቅላላ ብር 801.65 ቢሊዮን የወጪ በጀት ተደግፎ ቀርቧል፡፡ በዚህም መሠረት በታቀደው ገቢና ወጪ መካከል የብር ብር 281.05 ቢሊዮን ያልተጣራ የበጀት ጉድለት (gross budget deficit) የታየ ሲሆን፣ ይህንንም የበጀት ጉድለት ለመሸፈን ብር 39.01 ቢሊዮን ከውጭ ሀገር እና ብር 242.04 ቢሊዮን ከሀገር ውስጥ በድምሩ ብር 281.05 ቢሊዮን ያልተጣራ ብድር (gross borrowing) በመውሰድ ለመሸፈን ታቅዷል፡፡ የበጀት ጉድለቱን ለመሸፈን ለመበደር ከታቀደው ብር 281.05 ቢሊዮን ጠቅላላ ያልተጣራ የሀገር ውስጥና የውጭ ብድር ውስጥ ብር 53.7 ቢሊዮን የሚሆነው ተመልሶ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ዋና ብድር ክፍያ የሚውል በመሆኑ የተጣራ የበጀት ጉድለት (net budget deficit) መጠኑ ብር 227 ቢሊዮን ይሆናል፡፡ በመሆኑም የተጣራ የበጀት ጉድለት መጠኑ ከአጠቃላይ የሀገር ምርት ያለው ድርሻ 2.1 በመቶ ሲሆን፣ የተጣራ የሀገር ውስጥ ብድር ደግሞ ከአጠቃላይ የሀገር ምርት ያለው ድርሻ 2.2 በመቶ ነው፡፡ ይህም የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ እንዲኖር ለማድረግ ከተያዘው የፊሲካልና የገንዘብ ፖሊሲ ጋር የተጣጣመ ሲሆን፣ ከዚህ ከተያዘው ጠቅላላ ብድር ውስጥ ከፍተኛው ድርሻ የሀገር ውስጥ ብድር ከመሆኑ አንጻር በዋጋ ንረት ላይ የጎላ ተጽእኖ እንዳይፈጥር አብዛኛው ብድር የትሬዠሪ ቢልና የመካከለኛ ዘመን ቦንድ በመሸጥ ለመውሰድ የታቀደ ብድር ነው፡፡

### የተከበሩ አፈ ጉባኤ
### የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት

በአጠቃላይ ይህ ለ2016 ተደግፎ የቀረበው ረቂቅ የፌዴራል መንግስት በጀት ካለፉት ዓመታት በጀት ጋር ሲነጻጸር የልማት ፍላጎታችንን ለማሳካት በቂ ባይሆንም የተጀመሩ የልማት ፕሮጀክቶችን ለማስጨረስ የሚበቃ ሲሆን፣ የገጠሙንን የፊሲካል ተግዳሮቶች በማስተካከል በቀጣይ ጤናማ የፊሲካል አቋም እንዲኖረን ለማድረግ ወሳኝ መሆኑን በመገንዘብ ሁሉም የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ለትግበራው የበኩላቸውን ጥረት ማድረግ ተገቢ ይሆናል፡፡ ከዚህ አንጻር ባለበጀት መ/ቤቶች አስፈላጊውን ዝግጅት ሁሉ

በማድረግ የተመደበላቸውን በጀት ለታለመለት ዓላማ በቁጠባና በላቀ ውጤታማነት ጥቅም ላይ ማዋል ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለዚህም የሚጸድቀውን በጀት የመንግስትን የፋይናንስ፣ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ህጎችን ብቻ ተከትለው በጀቱን በቁጠባና በውጤታማነት ስራ ላይ ማዋል የሚገባቸው ሲሆን በገንዘብ ሚኒስቴር በኩልም አስፈላጊው ድጋፍ ሁሉ እንደሚደረግ እያረጋገጥኩ፣ በጀቱ በአግባቡ ሥራ መዋሉን ለማረጋገጥም አስፈላጊው የክትትልና የቁጥጥር ስራን በማጠናከር የተጀመረው ተጠያቂነትን የማረጋገጥ እንቅስቃሴ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡ በተጨማሪም ይህ የ2016 የፌዴራል መንግስት በጀት ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው የሀገር ውስጥ ገቢ አሰባሰብ ከሌላው ጊዜ የተለየ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት የታቀደውን ገቢ ስናሳካ ብቻ በመሆኑ ይህም የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ርብርብ የሚጠይቅ መሆኑን ለማሳሰብ እፈልጋለሁ፡፡ ለዚህም የተከበረው ም/ቤትም ሆነ የሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች የጀመሩት ድጋፍ ተጠናክሮ ዕገዛ እንዲደረግልን በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡

እንዲሁም ይህ የ2016 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት በጀት በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲሆን እየተመኘሁ፣ የበጀት ዝግጅቱ የተሳካ እንዲሆን የበጀት ጥያቄያቸውን በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳና በተዘጋጀው የበጀት ሥርዓት መሰረት ላቀረቡ አስፈጻሚ አካላት፣ በረቂቅ በጀቱ ላይ ሰፊ ውይይት በማካሄድና በመደገፍ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ወቅቱን ጠብቆ ለዚህ ምክር ቤት እንዲቀርብ በማድረጉ እንዲሁም የመገናኛ ብዙኃን ተቋማት የበጀት መረጃዎችን ለሕዝብ በማስተላለፍ ላደረጉት አስተዋጽኦ በመ/ቤቴ ስም ላመሰግን እወዳለሁ፡፡

በመጨረሻም ይህን ተደግፎ የቀረበውን የ2016 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት በጀት የተከበረው ምክር ቤት እንዲያፀድቀው በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡

## አመሰግናለሁ፡፡